# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ጥር 2002

## አዋጅ! አዋጅ! አስቸኳይ ጥሪ ለኢትዮጵያ ሕዝብ

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!**

**ውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ህልዋናዋ ለአስከፊ አደጋ ከተጋለጠ 19 ዓመት ደረሰ፡፡ ነገ ሁኔታዎች ይሻሻሉ ይሆናል በሚል ስንጠብቅ፤ አንዳንዴም ለወያኔ አደናጋሪ ልፈፋ ጆሮ ሰጥተን ስንደናገርናለወያኔ አገዛዝ ሰለባ ስንሆን ዓመታት አለፉ፡፡ አደባባይ ኢየሱስ፣ አንዋረ መስጊድ፣ አሰቦት፣ አርባጉጉ፣ ወተር፣ አረካ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ጋምቤላ፣ አጋዴን፣ አዲስ አበባ 1997 ስንት ሺ ህይወት ገበርን፡፡ ከ35 ሺ ያላነሱ ወገኖች ከቃሊቲ እስከ ዝዋይ፤ ከዴዴሳ እስከ ብር ሸለቆና ሸዋ ሮቢት ወዘተ ዛሬም ታግተው ስቃይን እየተቀበሉ ናቸው፡፡ ከትላንት ዛሬ መከራችንና ፍዳችን እየተባባሰና እየከበደ በመሄድ ላይ ነው፡፡ የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በተለይ አማራውና ኦሮሞውን ለመሰባበርና ለማድቀቅ ይሁነኝ ብሎ በጭካኔ እየሰራ ያለ መሆኑን ዛሬ የማያውቅ የለም፡፡ ሀገራችን ባለፉት 19 ዓመታት ለደረሰባት ሁሉ ተጠያቂው የወያኔ አገዛዝ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፡፡**

**አዋጅ አዋጅ የደበሎ ቅዳጅ ማለቱን አስገዳጅ ያደረገው የዛሬ ሁኔታ የሀገራችንን መሸጥ ይመለከታል፡፡ ሌላው ሌላው በደልማ ደርሶብናል፤ ደምተናል፤ ሀገር ስትዋረድ ስትገነጠልም አይተናል፡፡ ድምፃችን ተሰረቀ፤ ምርጫ ተጭበረበረ ባሉ ወገኖች ሲፈጁ አይተናል፡፡ የኑሮ ውድነት አድቅቆናል፤ ግማሽ ሚሊዮን በላይ ዜጋ መንገድ አዳሪ ሲሆን መቀበሉን ተገደናል፤ ረሀብ ጠብሶናል፤ የወያኔ ካድሬዎች ሲዘባነኑብን መቀበል ግድ ሆኖብናል፤ የዘረኞችን ግፍ ሁሉን ችለን ባጅተናል፡፡ አልፎም ወያኔ ለጦርነት ሲማግደን ተማግደን በ100 ሺ ደረጃ በባድሜም በሶማሊያም አልቀናል፤ ተሞኝተናል፡፡ ሐቁ ይነገር ከተባለም ወያኔን ተፋልመን ተሰውተናል፤ ታስረናል፤ ስየል ተቀብለናል፤ የእምቢኝን ሰንደቅ አውለብልበን የትግልን ሻማ ለኩሰን ቆይተናል፡፡ ያመናቸው ሲከዱን፤ ይመሩናል ያልናቸው ሲጥሉን፤ ተስፋ የጣልንባቸው ለቀቢፀ ተሰፋ ሲዳርጉን እግዚኦ እያልንና ነገ ይሻሻል ይሆናል እያልንም ቆይተናል፡፡ ምን ያልቻልነው፤ ምን ያልተሸከምነው ውርደትና መከራ አለ? ትዕግሥታችን ያተረፈው ነገር የለም፤ መጨመታችን የቀነሰልን መከራ የለም - ስቃያችን ተባባሰ እንጂ !**

**ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!**

**ውድ ሀገራችን ነፃነቷን ጠብቅና ተከብራ የቆየቸው በትግልና በመስዋዕትነት ነው፡፡ በልጆቿ የደም ግብር፡፡ ዛሬም ሀገራችን ህልውናዋን ጠብቃ ወያኔ ከዘረጋባት ወጥመድ ማምለጥ**

የምትችለው ዜጎቿ ከጥፋት ሊያድኗት ተባብረው ከተነሱ ነው:: ሌላ መንገድና መፍትሄ የለም:: በሥልጣን ያለው ጠባብ ብሔረተኛና ዘረኛ አገዛዝ ኢትዮጵያን ሊያወድም የመጣ ነው:: መለስ ዜናዊ፤ ስብሐት ነጋና መሰሎቻቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ናቸው፤ ኢትዮጵያን አምርረው ይጠላሉ፤ አማራውንና ሌላውንም ሕዝብ ማውደም ማዋረድ ይፈልጋሉ፤ የብሔረሰባቸውን የበላይነት ማረጋገጥ ይመኛሉ:: ከዚህ ሌላ ግን የወያኔ ቡድን ሕዝብን መጥላት ብቻ ሳይሆን ንቋል:: በኃይል አፍኜ ዕድሜ ልክ እገዛለሁ ብሎ ያምናል:: በመደለልና በሆድ በመግዛት ብዙዎችን አንበረክካለሁ፤ ተለጣፊና ሎሌ አደርጋለሁ ብሎ ተነስቷል--ሙከራውም ውጤት አልባ ቀረ ማለት አይቻልም:: የወያኔ ቡድን ዘረኛ ዕብሪት ከመሬት ተያይዞ በመጀመሪያ ሲከሰት የጎንደርን መሬት ፀለምትን (ዛሬ ምዕራብ ትግራይ የሚባለው)፤ ወልቃይትን (ሁመራን ጨምሮ) ጠገዴንና እስከ አብደራፊ ድረስ ያለውን መሬት የትግራይ ብሎ ጠቀለለ:: ይህን በተመለከተ የተከሰተው ተቃውሞ አፋዊ ብቻ ከመሆን ባለማለፉ ወያኔ በዕብሪቱ ገፋበት:: ለትግራይ ግንጠላ ዕቅዱ በመዘጋጀትም በዚህ መልክ ከሱዳን የሚዋሰን ሆኖ ቁጭ አለ:: ከወሎም እንዲሁ መሬት ዘረፋውን አጧጧፈ:: ከራሱ ክልል ውጪ ኢትዮጵያ ብትሸነሽን ግድ የለሹና የግንጠላን አንቀፅ ሕገ-መንግሥት በሚለው ሰነዱ ያስገባው ወያኔ÷ ሱዳንን አገባብቶ ለመያዝ በሚል በስንት ደምና ህይወት ተከብሮ የቆየውን ሰፊ መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሰጥቶ እነሆ ዛሬ ስንቱ ጀግና ህይወቱን በገበረባት ቋራ የሱዳን ጦር ሰፍሮ ይገኛል:: ይህን በተመለከተም በቂና የጎላ ተቃውሞ እንዳይደረግ ሻጥር ፈፅሞ፤ ህይወቴን ለህገሬ የሚል ዜጋ ያለቀ አስመስሎ ታሪካዊ ከህደት ፈፅሞ አዋረደን::

ረሀብ÷ በሽታ÷ መከራ ስቃዩ ያክትም ማለቱ ተገቢ ቢሆንም ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ተጋፍጣ ያለው ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ የተለየና የሀገራችንን ህልውና የሚመለከት ነው:: የመለስ ዜናዊ ቡድን ሀገራችንን በጠራራ ፀሐይ ለባዕዳን እየሸጠ ነው:: ይባስ ብሎ በአባይ ወንዝ የተነሳ ለዘመናት ኢትዮጵያን ለመውጋት ወይም ለማዳከምና ለማበጣበጥ ስትጥር ለቆየቸው ግብፅም ሳይቀር - ያውም በባሕር ዳር - መሬት መሸጡን ቀጥሏል:: ይህ ከሀዲና ዘረኛ ቡድን የኢትዮጵያን የኃይል ማመንጫ ተቋሞች ለግብፅ ሊሸጥ ተነስቷልም እየተባለ ነው:: በአባይ ወሀ አጠቃቀም ላይም ከሀዲው መለስ ዜናዊ ከግብፅ ጋር ስምምነት በመፈራረም የኢትዮጵያንና የሌሎች የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ብሄራዊና ፍትሀዊ ጥቅም አሳልፎ ሰጥቷል:: ከሁሉም የከፋው ግን ለዘመናት ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችው ኢትዮጵያ በከሀዲው ወያኔ አማካኝነት ለአዲስ ዓይነት ቅኝ አገዛዝ ቀስ በቀስ እየተዳረገች፤ እየተሸጠች መሆኗ ነው:: ለም መሬቶቿ በባዕዳን ተይዘው፤ ምርቶችዋ ወደ ባዕድ እየተጓጓዙ፤ ሕዝቧ ምግብም ክብርም ተነፍጎ የሚሰቃይበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው::

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

መከታ ጋሻዬ፡ እናቴ ያልናት ኢትዮጵያ በከሀዲ የወያኔ መንጋ ስትሸጥና ስትዋረድ እስከመቼ በዝምታ እናያለን? ከዚህስ የበለጠ ውርደት ከየት ሊመጣብን ይችላል? ሀገራችንን ካጣናት በምንስ እንተካታለን? ወያኔ በከፋፍለህ ግዛ እርስበርስ አጋጭቶን ሁላችንንም ሀገር አልባ ሊያደርገን ቆርጦ ከተነሳ ውሎ አድሯል? የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ከሆኑና የዚችን የጀግና ሀገር ውርደት ከሚመኙ ጋር ባንዳው ወያኔ ገጥሟል:: አደብ ይገዛል፤ ኢትዮጵያዊነት ያድርበት ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅ ቡድን አይደለም:: በወያኔ የተጀመረው የሀገር ሽያጭ ብዙ ሳይጓዝ በአጭር መቅጨት ያስፈልጋል:: በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በዚህ ሀገር አድን ዘመቻ መሰለፍና መተባበርም አለበት:: ዝምታና ቸልተኛነት ለወያኔ ቡድን ጠቅሞ ኢትዮጵያን ያጠፋል:: ስለዚህም ኢሕአፓ በዚህ ታሪካዊ ወቅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስተላልፈው ጥሪ ሀገራችንን ለማዳን፤ ለማስከበር እንነሳ የሚል ነው:: ሀገራችን ተሸጣ ሳታልቅና በገዛ ሀገራችን ቅኝ ተገዢ ሳንሆን በፊት መነሳትና መቃወም አለብን:: እያንዳንዱ ዜጋ ሊወስድ የሚችለው እርምጃ ብዙ ነው:: በወያኔም ሆነ መሬታችንን ሊቀሙን በተነሱት ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰዱ የወያኔን ዕቅድ በእንጭጩ ያስቀረዋል:: ኢሕአፓ ለሀገር አድን ትግሉ ዝግጁ ከሆኑት ጋር ሁሉ ለዚህ ግዳጅ በመተባበር ሊታገል ዝግጁ ነው:: በባዕድ ሀገር ያሉ ዜጎችም ይህንን የወያኔ ክህደት እያጋለጡ ሀገርን ለማዳን ሊዋደቁ ለተዘጋጁት ሙሉ ድጋፍን እንዲያደርጉ፤ ቁጭቱና ኡኡታው በተጨባጭ ተግባር - ሀገር አድን ትግሉን በመርዳትና በማገዝ - እንዲተካ ያሳስባል::

ኢትዮጵያ የምትገኝበት ሁኔታ ከበፊቱ ሁሉ የተለየ ነው:: ባዕድ ወሯታል:: ባዕዳን መሬቷን እየተቀራመቱ ናቸው:: ከሀዲና ባንዳ ቡድን ሰፍሮባታል::

ሀገራችንን ለማዳን አምፀን እንነሳ::
ልንወስድ የምንችለውን እርምጃ በተናጠልም ሆነ በጋራ እንውሰድ::
የኢትዮጵያ ጀግና ልጆች ዛሬም አሉ የሚለውን መልዕክት ለወያኔም፤ ለወራሪዎችም እየቀጣን እናስተምራቸው::

ኢትዮጵያን እናድን!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France